# ግልፅ ጥያቄዎች ለአቶ መለስ ዜናዊ

### ከመብረቁ ዘቋራ

የሕወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ እንደተከፋፈለ "በአብዮታችን መታደስና መበስበስ መካከል የተፈጠረው ወሳኝ ልዩነት" በሚል ርዕስ በአቀረቡት ዘገባ፡

**ጥቅስ 1፡**

"ድርጅታችን በሰዎች ቀረቤታ በመጠቃቀም ትስስር ላይ እየሆነ መጣ። የሰዎች ምደባና ዝውውር ወዘተ ግልጽ መሆኑ እየቀረ፣ በትውውቅ፣ በመቀራረብ፣ በእከከኝ ልከክኽ የሚወሰን እየሆነ መጣ። ግምገማ፣ ሂስ፣ ወዘተ ቁለልቁል ብቻ እንጅ ሽቅብ የማይመለከቱ ያልተፈለጉ ሰዎችን ለማስወገድ ታልመው የሚካሄዱ ወይም ደግሞ ለፈፃሚዎች የማቸፍቸፍ ፀረ-ዴሞክራሲ ባህሪ እየያዙ መጡ"

ብለው ነበር። አሁንስ ከአስር ዓመት በኋላ ምን የተለወጠ ነገር ዴሞክራሲያዊ አሰራር አለ?

**ጥቅስ 2፡**

“ድርጅታችን በግልጽ አሰራር ህግና ስርዓት ላይ ከተመሰረተ ድርጅት ወደ በሰዎች ፍላጎት፣ ምኞት፣ ቅርርብና ትስስር የተመሰረተ ሃይል እየተቀየረ፣ እየበሰበሰ፣ ባህሪው እየተለወጠ መጣ።"

ብለዋል። ከዚህ መበስበስ፣ አሁንስ ተፈውሷል ወይ?

**ጥቅስ 3፡**

“በአንዳንዶች ዘንድ ቅንጣት ይሉኝታ የሌለው የመንግሥትና የሕዝብ ንብረት ዘረፋ ተካሂደ። ድንገት ሚሊዬነሮች ከዓለት ሥር ይመነጩ ጀመር። መንግሥታዊና ድርጅታዊ ሃላፊነት ወደማትነጥፈው ታላቢ ላም ተቀየሩ። አንዳንዶቹ ራሳቸውንና በራሳቸው ሰዎች በኩል ሲዘርፉ፣ ሌሎች ደግሞ ዝርፊያውን መራቂ፣ ጠባቂ፣ ተከላካይ ሆኑ። ስልጣን ሀብት ማካበቻ፣ ስልጣን ዘላለማዊ ርስት አድርጎ ማየትና ጥቅም ላይ ማዋል ተከሰተ። ድርጅታችን ከጭንቅላቷና ከእንጥሏ መግማት ጀመረች። ድርጅታችን እየገማች መሆኗን ያሸተተ ካድሬ እየበገነ ወደውስጥ መተንፈስ ካልሆነ በስተቀር፣ ማድረግ የሚችለው ነገር አልነበረም።"

ብለው ዘግበዋል። ለመሆኑ አሁንስ የጭንቅላቷና የእንጥሏ መግማት የባሰባት አይመስለዎትም? ወይስ አይሰማዎትም?

**ጥቅስ 4፡**

“በድርጅታችን ውስጥ የተከሰተው መበስበስ የሥርዓታችን ወሳኝ ሞተር በሆነው ሃይል የተፈጠረ ስለሆነ፣ ሣንካው በድርጅቱ ውስጥ ብቻ ተገድቦ መቅረት አልቻለም። ሕዝባችንም ቀስ በቀስ የሹመኞች ጉቦና ፍጥጫ ሰለባ እየሆነ መጣ። ፍትኅና ርትዕ እየተጓደለ፣ እንደየሰው፣ እንደየቅርበትህ፣ እንደየገንዘብህ፣ መኖር ሆነ። ሕዝብ በነፃነት ተወያይቶ፣ የሚፈልገውንና ከልብ ያመነበትን ብቻ እየወሰነ፣ የቀረውን ውድቅ የሚያደርግበት ተሳትፎ ሳይሆን፣ የሚያምንበትንና የማያምንበትን ቀላቅሎ ያስገዳጅነት ያህል የሚፈፅምበት፣ ቀስ በቀስ ውስጡን የሚያቅረው ሁኔታ መፈጠር ጀመረ። ሳይሳቀቅ የመሰለውን ተናግሮ፣ ተኝቶ የሚያድርበት ሳይሆን መትሮና ለክቶ የሚናገርበት፣ ’ምን ብናገር ደስ ይሰኙልኛል?’ የሚል ስሌት ከአንጎሉ እያመዛዘነ መናገር የሚጀምርበት ሁኔታ እየተፈጠረ መጣ።"

በተለይ ይኽ ጥቅስ ፈፅሞ አያሳፍርምን? እሥር ቤቱን የሞሉት ጋዜጠኞችና ተቃዋሚዎች ሃሳባቸውን መግለጻቸው እንደሽብር ተቆጥሮባቸው አይደለምን? ያሳዝናል!

**ጥቅስ 5፡**

"መበስበሱ በድርጅታችን በሕወሓት ብቻ ሳይሆን በሌሎች ወዳጅ ድርጅቶችም እየበረታ ስለሄደ የህብረተሰቡን የበለጠ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አቅም ከጎናችን ማሰለፍ አልቻልንም።"

ብለው ነበር። ታዲያ ህዝቡ ዘጠና ዘጠኝ ነጥብ ስድስት በመቶ ስለደገፈ ለሥልጣን በቅተናል እያላችሁ ታሾፉላችሁ! በምን ተዓምር ነው ከጎናችሁ የተሰለፈው? የህዝቡ ከእናንተ ጋር ሆድና ጀርባ መሆን ከመቸውም ጎልቶ እንደሚታይ አይሰማችሁምን?

**ጥቅስ 6፡**

"በአጭሩ ድርጅታችን እየበሰበሰች፣ የሥርዓታችንና የአመራራችን ባህሪ እየተቀየረ፣ ሙስናና ፀረ-ዴሞክራሲ ያልጠራ ድሪቶ አስተሳሰብ እያንሸራተተን፣ ቁልቁል ወደአዙሪት መሄድ ጀመርን።"

ብለውናል። አዎ! ታዲያ ከዚህ አዙሪት የወጣችሁ ይመስላችኋል ወይ? ሙስና በሀገሪቱ ላይ ከመቼውም በተባባሰ ሁኔታ በአለበት ሥርዓት ውስጥ አይደለንም ወይ?

ይኽ ሁሉ ችግር የተፈጠረው ሻል ያሉት በስባሶች የጭዳ ዶሮ ሆነው፣ አናታችሁና እንጥላችሁ የገማችሁት በሥልጣኑ ላይ ስለቀራችሁ ስለሆነ፣ የሚከተለውን ግጥም አበረክትላችኋለሁ፡

**<u>እንጥሏ በስብሶ አናቷ ሲገማ</u>**

ያንጊዜ ማሌሊት፣ በውስጥ ግምገማ፣
እንጥሏ በስብሶ፣ አናቷ ሲገማ፣
ከፓርቲው አመራር፣ ከበሰበሱቱ፣
መለስ አይደለም ወይ? የገማው አናቱ?!

ታዲያ መለስተኞች፣ በስባሶች ሲሻሩ፣
የገሙት በብዛት፣ ከውስጥ ስለቀሩ፣
ግማግም፣ በስባሳ፣ አብሮ እያዘገመ፣
ብስብሱን ከጥንቡ፣ እያጠራቀመ፣
ይኸው! የብስብሶች፣ የግም ተሃድሶ!
ሀገርን በክሏል፣ ዳር እሰከዳር ነግሶ።

የወያኔ ሥልጡን፣ የወያኔ ምልምል፣
በሙሉ ብስብስ ነው፣ ከግም የሚበቅል።

ተማሪ፣ አስተማሪ፣ ገበሬ፣ ወታደር፣
ነጋዴ፣ ደላላ፣ ሊስትሮ፣ ስርቶ አደር፣
የግሙ ኢሕአዴግ፣ ምልምል የሆናችሁ፣
መበስበሳችሁን፣ ማወቅ አለባችሁ።

EthioLion.Com

ብስብስ ከግማግም፣ እየተጣቀሰ፣
በግም ተሃድሶ፣ ሀገሬ ፈረሰ!
ሀገሬ ፈረሰ! በነሲብ ተሸጠ!
ሙስና ነገሰ፣ ድህነት አበጠ!

ፍትህ፣ ርትዕ ጠፋ፣ ቅጥፈት ባህል ሆነ፣
አንድነት ተናጋ፣ እምነት መነመነ፣
ገምቶ የመነጨው፣ ከግሌሊት አናት፣
ብስብስ ከበስባሳ፣ ሀገሬን አገማት!

የመለስ ደጋፊ፣ በቆላም በደጋ፣
በውስጥም በውጭም፣ ያለህ ምልምል ዜጋ፣
በስባሳ መሆንክን፣ እንዳትዘነጋ።
ሌሎችም ወገኖች፣ እንዳትበላሹ፣
ንቁ፤ አትነካኩ፤ ከበስባሶች ሽሹ።
የኢሕአዴግ ሥርዓት፣ ድሩም ሆነ ማጉ፣
ግማግም በስባሳ፣ መሆኑን አትዘንጉ!
በያላችሁበት፣ መፍትሄ ፈልጉ።

ይኸ በስባሳ ሥርዓት፣ ጨርሶ በስብሷል፣
ሁሉም አሸባሪ፣ መስሎ ይታየዋል፣
ያለ ቢመስለውም፣ በቁመናው ሞቷል።

EthioLion.Com